<u>የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ላነሷቸው ጥያቄዎች ከዩኒቨርሲቲው ሴኔት የተሰጠ ግብረመልስና ውሳኔ</u>

መግቢያ

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በተለየ መልኩ በተሰጠው ተልዕኮ መሠረት በ14 የትምህርት ዘርፎች አሳታፊና ተለማጭ (Flexible) ሥርአተ ትምህርት ቀርጾ ስራ ላይ ያዋለ ሲሆን፤የሥርአተ ትምህርቱም ዋና ግብ በአፕላይድ ተፈጥሮ ሳይንስና ምህንድስና ጥራት ያለዉ ትምህርት በመስጠት፣ ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንዲሁም በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሚሆኑ ምሩቃንን ማፍራት ነው፡፡

ይህንን ተልእኮ ለማሳካት በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ቅበላ መስፈርት መሠረት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ተቀብሎ እያስተማረ የሚገኝ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲዉ በዉጭ አገር ዜጋ ሲተዳደር በነበረበት ወቅት የተለያዩ ቃሎች እንደተገቡላቸው በመጠቆም ነገር ግን ቃል የተገቡልን የሚሏቸው ጉዳዮች ካልተሟሉላቸው በስተቀር ትምህርት እንደማይቀጥሉ በጽሁፍና በተለያዩ መድረኮች ላይ በቃል በመግለጽ ከአስር ቀናት በላይ በትምህርት ገበታቸው ላይ አልተገኙም፡፡

ተማሪዎቹም ከህዳር 15/2011 ዓ.ም ጀምሮ በጽሁፍና በቃል ያነሷቸው አንኳር ጥያቄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1ኛ- ለመቶ ፐርሰንት ምሩቃን የስራ ቅጥር እንዲሰጣቸው

2ኛ- ቢያንስ 90 በመቶ ከተቻለ ደግሞ ለሁሉም ምሩቃን በተለያዩ የዉጭ ሃገራት ዉስጥ የድህረ ምረቃ ትምህርት ዕድል እንዲሰጣቸው

3ኛ- እስከ 54 በመቶ ለሚሆኑ ምሩቃን የፒ.ኤች.ዲ ትምህርት እድል እንዲሰጣቸው

4ኛ- ለሁሉም ተማሪ ላፕቶፕ ኮምፒዉተር በነፃ ወከፍ እንዲሰጣቸዉ

5ኛ- የኢ-ሌርኒንግ ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ በማንኛዉም ሰአት በየዶርሙ መጠቀም እንዲችሉ እንዲደረግላቸው

ሙሉ በሙሉ ማስተንጎላቸው ፊዕሞ የተክለከለ መሆኑ በጥልቀት የተረዳና ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ቢገነዘብም የተማሪዎቹን የወጣትነት እድሜ ባህሪን፣ የአገሪቷን ነባራዊ ሁኔታና ምናልባትም የተወሰኑ ተማሪዎች ተፅእና የሌሎች አካላት እጅ ሊኖርበት እንደሚችል ከግንዛቤ በማስገባት ምንም እንኳን ጥያቄ መጠየቅ ዲሞክራሲያዊ መብት ቢሆንም ትምህርት አቁሞ መሆን እንደሌለበት አፅንኦት በመስጠት የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል።

1ኛ. ከሰኞ ታህሳስ 1/2011 ዓ.ም ጀምሮ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመለሱና ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆነ ተማሪ ግን በገዛ ፈቃዱ ትምህርቱን እንዳቋረጠ ተደርጎ እንደሚወሰድና ግቢዉን ለቆ እንዲወጣ እንዲደረግ

2ኛ. ወደ ትምህርት ገበታቸው መመለስ የሚፈልጉ ተማሪዎች ላይ ማንኛዉንም አሉታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር የሚሞክሩ ተማሪዎች ቢኖሩ ህጋዊ የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ

3ኛ. ወደ ትምህርት ገበታቸው የሚመለሱ ተማሪዎችን ደህንነት በአግባቡ መጠበቅ እንዲቻል ተመጣጣኝ የጥበቃ ኃይል እንዲሰማራና አስፈላጊው ከለላ እንዲደረግላቸው

4ኛ. ተማሪዎቹ ወደ መደበኛ የትምህርት ገበታቸዉ እንዲመለሱ የዩኒቨርሲቲዉ አመራርም ሆነ ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች የሄዱበትን ሂደት ሁሉ በመገናኛ ብዙሃንና በማህበራዊ ሚዲያዎች፣ እንዲሁም በማስታወቂያዎች ለህዝብ እንዲገለፅ ተወስኗል።

በተጨማሪም የተማሪዎች ወላጆችና የአከባቢው ማህበረሰብ ተማሪዎቹ ወደ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲመለሱ አስፈላጊውን ምክርና ተግባዕ እንዲያደርጉ ጥሪ እያቀረብን ይህንን አስመልክቶ ሴኔቱ ያስተላለፈዉ ዉሳኔ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርም ዕዉቅና ሊኖርው ስለሚገባ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዲቀርብ አቅጣጫ ተሰጥቷል።